መንፈሳዊ ቅኔዎች

ጫጩት ከበዛበት አደርኩኝ ገብቼ፤
አዬ ልብ ማጣት ቅንቅኑን ረስቼ።።

አጠረ ቁመቴ ወዳጆቼን ባይ፤
እያደሩ ማነስ ለካ እንዲህ ነው ወይ።።

ከአቤል ዝምሮ ነበር የታመነ፤
አሁን ግን ስናየው ሞት ቀጣፊ ሆነ።።

ሰው ሁሉ በርስቱ ይጨርሳል ሀብቱን፤
የኋላ የኋላ ላያጣው መሬቱን።።

ወይ አላሳጨድነው ወይ ከብት አልበላው፤
ከቶ መቼ ይሆን ያ ሣር ማሊያው።።

ብላጨው አመመኝ ብሠራው ከፋኝ፡
አንድ ራሴ እኮ ነው የሚያስጨንቀኝ።።

የኩዳዬውስ ጾም አላስጨነቀው፤
ሰዉ የተጎዳው በህማማቱ ነው ።።

በባላገር ነበር ኑሮስ የሚሻል፤
ከተማ ሰው ገብቶ ምን ሰው ይሆናል።።

የኔማ ዘመዶች ምን አጡ በሙሉ፤
መልካም በቅሎ ነበር ፈረስ ፈረስ አሉ።።

አዲስ ቤት ስትሠሩ ባለ ጉልላት፤
ማዘን ጨምሩበት እንዲሰነብት።።

ተካፈሉት አሉኝ እቴ የኛን እጣ፤
የትም ሀገር ብንኼድ በይ መሬት አናጣ።።

ቤቴን መንገድ ዳር ሠርቼው ቅር አለኝ፤
አላፊው አግዳሚው ያፈር ሰው መሰለኝ።።

ዳዊቴን ወሰደው የማላውቀው ልጅ፤
የማይቀር ገንዘቤን ደግሞት ይስጠኝ እንጂ።።

ይገኝ መስሎኝ ነበር የመጣን ከተማ፤
እንግባ አገራችን እውነት ከጠፋማ።።

ድጓ ጾመ ድጓ ተሰቅሎ ከቤቴ፤
እኔስ የሚገርመኝ ሳልማር መቅረቴ።።

የራበው ካልበላ እንደምን ይሆናል፤
ከዚያ ወዲያ ጦም ነው ማማት ይገምራል።።

ተካፈሉት አሉኝ እቴ የኛን እጣ፤
የትም ሀገር ብንኼድ በይ መሬት አናጣ።።

እውነትን ሳይጨብጥ ሙግት የያዘ ሰው፤
ዛሬ አለሁ አለሁ ቢል ነገ ለማፈር ነው።።

ከወጥ ቤት ገባሁ ድንገት፤
ቋንጣ ጠብሼ ለሙበላት፤
ወድቄ ነበር ከሳት ላይ፤
ሥጋ ሥጋዬን ሳይ።።

የልጅ አገረድ አውታታ፣
አውራ መንገድ ላይ ተኝታ፣
ተነሽ ቢሏት ምነው፣
ይህ ሁሉ አለማፈር ነው።።

ሰው ሁሉ በሆዱ ጠጅ እያማረው፤
እግዚአብሔር ጠላና እንጀራ ነሳው።።

አልታገልህም ግራ ካገባኸኝ፤
ደግሞ ማፈር አለ ከሰው ፊት ጥለኸኝ።።

ሌሊት ከጭቃ ለይ ፈረስ ቢጥልህ፤
ወንድሜ አትጨነቅ ማንም አላየህ፤
ይልቁን ተጠንቀቅ ቀን እንዳይጥልህ።።

ከወዲያ ወዲህ ተጣርተው፤
ሙታን በአንድ ላይ ተሰብስበው፤
ያጫውታሉ የሞቱት ቁመው ለሚሔዱት።።

በዘንድሮ ዘመን ፀሐይ በጣም በረታብን፤
ይዘግይ እንጂ እስኪዘንብ ደመና ሆኖ አይቀርም።።

መርዛም ሆነ አሉኝ ብዕር፣ የምሁራን ምሳር፤
የመርማሪዎች ምክር፣ ያገር መድኃኒት ማሰር።።

ጎድን ተዳቢቱን ተብትበህ ጥበሰው፤
እስኪ በል ሀሞቱን አያውቅምና ሰው።።

ሠርቼ ሠርቼ አዳራሽ ከእልፍኝ፤
በማለቂያው ጌዜ ላፈርሰው ሆንኩኝ።።

ሸንበቆን ግድግዳ ማገር ከመቁረጥ፤
ማዘን ቤት የሠራል የማይናወጥ።።

ሸማነኔው ሰውዬ ችግር ሳይገባው፤
አንድ አርብ ቢኖረው ለሥጋ ሸጠው።።

መልካም ቤተልሔም መልካም ደጀ ሰላም፤
እኔ አምላክን ብሆን ላፈረሰው አልሠራም።።

ደርቦ መልበሱ አሁን ለምንድ ነው፤
ሁሉም መነጠሉ መለየቱ አይቀር ነው።።

ቤት ከገቡ ወዲያ ሌት ከሚዘንበው፤
መጨነቅ ያለብን ቀን ለጣለው ነው።።

ሌሊት ከጭቃ ላይ ፈረስ ቢጥልህ፤
ወንድሜ አትጨነቅ ማንም አላየህ፤
ይልቁን ተጠንቀቅ ቀን እንዳይጥልህ።።

ከሹሙም ከአዋቂም መጋጨቱን ተውኩኝ፤
እርሱ ነው ስላሉኝ አፍራሽና ሠሪው።።
አምላክ ድህነቱ መች ጎጆ ያሠራዋል፤
እዛም እዚህ እያለ ካመኑት ቤት ያድራል።።

የእናት ልጅ ነበር ስከፋ የሚከፋው፤
ቆርጦ አይቀርም ነበር አንተ ባትጠራው።።

ረቂቁ እሔዳለሁ ተጓዥ ነኝ ያለ ሰው፤
ተቀበዩን ያጣል ጠብቀኝ ካላለው።።

እባክህ አምላኬ አንተ ስጠኝ መላ፤
አብረን አንብላ ያሉት ዞሩ እንዳያባላ።።

ልም ገዝቻለው ጥገት፤
እጠጣ ብዬ ወተት፤
ቅሉ ተሰብሮ አዝናለሁ፤
በምን አልባታለሁ።።

በለሳን ደግ አገር የሚል ሰው ማን አለ፤
በለስ አይደለም ወይ እኛን የገደለ።።

ቁጠሩ ቢሏቸው የሳምንቱን ቀናት፤
ስድስቱን ጠሩና ዕረቡን ገደፏት።።

አምላክ ግብር ጠርቶ ያበላል ይላሉ፤
በምድር ቀሪ የለም ሁሉም የጠራሉ፤
አምላኬ ግብርህን እንዳታሳነሰው፤
አምቢ ብሎ አይቀርም አንተ የጠኸው ሰው።።

የአዲስ አበባ መሬት አያውቅም ቡና በቅሎበት፤
መቼም መቼም አንውልም ሳንጠጣው፣
የከፋን ሳንቀመሰው።።

በልቼ ጠጥቼ ገባሁኝ ከፍዳ፤
አላልቅልህ ብሎኝ የሄ የሥጋ እዳ።።

በሬዬ ጠፍቶብኝ ስባዝን ስባጅ፤
እውነት ከጠፋማ አምላክ ይፍረድ እንጂ።።

ለሠሪው ለመስጠት አፈሩን የጐለሁ፤
ገል አፈር መሆኑን ተረድቼዋለሁ።።

ሌላ እቃ ከሰው ቤት ምን አስዋሳችሁ፤
በቤት ሙሉ አናንተ እያለቃችሁ።።

ለሁት ወር ኹዳዴን አጥርተው ጾመው፤
በውኃ ገደፉት ሥጋው ትተው።።

መልካም ልጃገረድ ቆማለች ከበር፤
እረቁቷን ሆና ወይ አለማፈር።።

ዳዊት ያልተማረ ፊደል ያልቆጠረ፤
መውደቂያው የት የሆን ቀድሞ ያልተማረ።።